እሱም "ለአንዳንድ ወጪዎችና ለጦርነቶች ውሏል" አላቸው። የመጣው በቅርብ ነው። ንብረቱም በጣም ብዙ ነው። በቅርቡም ምንም ዓይነት ጦርነት አልተካሄደም። እናም "ንብረቱ የመጣው በቅርቡ ነው። ብዙ በመሆኑም በዚህ ፍጥነት ሊያልቅ አይችልም" አሉት። አይሁዱ ሰውዬም "ንብረቱም ጌጡም አልቋል" አላቸው። እንደዋሻቸው አወቁ። ከብዙ ባልደረቦቻቸው መካከል ዙበይር ኢብኑል አዋምን ጠሩና "ዙበይር ቅጣትህን አቅምሰው" አሉት። ዙበይር ወደ ሰውዬው ሄደ። ሰውዬውም እጣ ፈንታው የከፋ እንደሚሆን በማሰብ እየተንቀጠቀጠ "አንድ ቀን ሁየይ ወደዚህ ቤት ሲገባ አይቼዋለሁ" በማለት ወደ አንድ ጭር ያለ አሮጌ ቤት ጠቆመው። ንብረቱ ተደብቆ ተገኘ። ነብዩ ዙበይርን ለዚህ ስራ ተጠቀሙበት።

የባልደረቦቻቸው የእርስ በርስ ግንኙነትም ተመሳሳይ ነበር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሞት ሲቃረቡ ህመሙ ጠናባቸውና ሶላት መምራት አልቻሉም። እናም "አቡበክር ያሰግዳችሁ" አሉ። አቡበክር ሆደ ቀጭን ነበሩ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የቅድመ ኢስላም የድንቁርና ዘመን እንዲሁም የወርቃማው የኢስላም ዘመን ጓደኛቸው ናቸው። የዱንያም የአኼራም ጓደኛቸው። እናም በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ህመም ውስጣቸው አዝኗል። ይሆንን የነብዩን ንግግር የሰሙ ሰዎች "አቡበክር ሆደ ቀጭን ናቸው። ይህን ቦታ ከሰጠናቸው እያለቀሱ ሰውን በትክክል ማሰገድ አይችሉም" አሏቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አቡበክርን ያወቋቸዋል። ሆደ ቀጭንና በቀላሉ እንባቸው የሚወርድ ሰው ናቸው። በተለይ የዚህ ዓይነት ነገር ሲያጋጥም። ሆኖም ከሳቸው ቀጥሎ ኸሊፋነቱ የሚገባው ለአቡበክር እንደሆነ እያመላከቱ ነው። ከእንግዲህ እኔ የለሁም። ኃላፊነቱን አቡበክር ይውሰድ ማለታቸው ነበር። እናም በድጋሚ "አቡበክር ያሰግዳችሁ" አሉ። አቡበክር እንደምንም አሰገዱ። ምንም እንኳ አቡበክር ሆደ ቀጭን ቢሆኑም አንዳንዴ ይቆጡ ነበር። ባልደረባቸው ኡመር ይህን እውነታ ያውቃሉ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሞቱ በኋላ ሙሃጂሩንና አንሷሮች ኸሊፋነቱን ለመወሰን በኑ ሰኢድ ላይ ተሰባሰቡ። ኡመር አቡበክርን ተከትለው ሄዱ። ኡመር እንዲህ ይላሉ፡- "በበኑ ሰዕድ የመወያያ ማዕከል ደርሰን ቁጭ እንዳልን አንድ አንሷር ሸሃዳ አደረገና አላህን ካመሰገነ በኋላ "እኛ የአላህ ረዳቶችና ግንባር ቀደም ሙስሊሞች ነን። እናንተ ሙሃጂሮች የኛ አካል ናችሁ። አንዳንዶቻችሁ በጥድፊያ የመሪነቱን ቦታ ልትወስዱብን ትፈልጋላችሁ" አለ። ሲጨርስ ለመናገር ፈለግኩ። የምናገራቸውን አንዳንድ ቃላት አሰብኩ። የምናገረው አቡበክር ባሉበት ነው። አቡበክር አንዳንዴ ኮስተር እንደሚሉም አውቃለሁ። "ኡመር ተረጋጋ" አሉኝ። ላበሳጫቸው አልፈለኩም። ደግሞ ከኔ በእውቀት የተሻሉ መሆናቸውን አውቃለሁ። ወላሂ እኔ ልናገር ያሰብኩትን ነገር ነው የተናገሩት። እንደውም ከኔ በተሻለ ሁኔታ።"

"የጠቀስከው በውስጥህ ያለው ጥሩ ነገር ያ ሐቅ ነው። ይሁንና አረቦች

በመሪነት የሚያውቁት ቁረይሾችን ብቻ ነው። በዘርም ሆነ በጎሳ ከአረቦች ይበልጥ ሚዛናዊ ናቸው። ከነሱ ውስጥ ሁለት እጩዎችን መልምያለሁ። እናንተ የምትፈልጉትን ምረጡ" አሉ የእኔንና የአቡ ኡብይዳን እጅ ወደ ላይ በማንሳት። ከዚህኛው ውጪ ንግግራቸውን አልጠላሁትም። ወላሂ እኔ አቡበከር ያሉበትን ህዝብ ከምመራ ሌላ ኃጢያት ሰርቼ አንገቴ ቢቆረጥ ይሻለኛል። አንድ አንሷር ተነሳና "እኔ በምከሬ ለሰዎች እፎይታን የምሰጥ ሰው ነኝ። የሚረዳኝና የሚጠብቀኝ ደህና ቤተሰብ አለኝ። ቁረይሾች ሆይ! እናንተም የራሳችሁ መሪ ቢኖራችሁና እኛም የራሳችን መሪ ቢኖረን ምን ይመስላችኋል?" ሲል ጠየቀ። ብጥብጥ ይነሳል ብለን እስከንፈራ ድረስ ህዝቡ ተንጫጫ። እኔም "አቡበከር ሆይ እጅዎትን ያውጡ" አልኳቸው። እጃቸውን አወጡ። ድጋፌን ሰጠኋቸው። ሙሐጂሮችም ደገፉ። አንሷሮችም ተከተሉ።

አዎ! የእያንዳንዱ ሰው ልብ የሚከፈትበት ልዩ ቁልፍ አለው። ፍቅሩን አግኝ። ተፅዕኖ አሳድርበት። ይሀን በተደጋጋሚ በህይወታችን ላይ እናየዋለን። በቢሮ አካባቢ ሠራተኞች ማናጀሩን ለሆነ ጉዳይ ከፈለግከው እከሌን ላከበት ወይም እከሌ በጣም ስለሚቀርበው እንዳንተ ሆኖ ያናግርልሃል ሲባል ሰምተህ ይሆናል። ለምን የራስህን ጥበብ ተጠቅመህ የሰዎችን ልብ መክፈት አትችልም? ጅራት ከመሆን ይልቅ ለምን ራስ መሆን አትችልም? አዎ! ጎበዝ ሁንና የእናትህን፣ የአባትህን፣ የሚስትህንና የልጆችህን ልቦች ቁልፍ ፈልገህ ከፈት። በስራ ቦታ ላይ አለቃህንና የስራ ባልደረቦችህን ልብ መክፈቻ ቁልፍ ፈልገህ አግኝ። የሰዎችን ልቦች ቁልፍ ማወቅህ ምክርህን እንዲቀበሉ ያደርጋቸዋል።

አንድ ቀን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጊድ ውስጥ ከባልደረቦቻቸው ጋር በመወያየት ላይ ሳሉ አንድ የገጠር ሰው መስጊድ ውስጥ ገባና ግራና ቀኝ ይመለከት ጀመር። ከዚያም ወደ መስጊዱ አንድ

ማዕዘን ሄዶ ሱሪውን አወለቀና ሸንቱን ይሸና ጀመር። ሶሃቦች ሰውዬው እንዴት መስጊድ ውስጥ ሸንቱን ይሸናል በሚል በጣም ተናደዱ። እናም ሮጠው ሄደው ሊመቱት ፈለጉ። ሆኖም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "አታቋርጡት!" በማለት እንዲረጋጉ ጠየቋቸው። ሶሃቦች ዝም ብለው ተመለከቱት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን መሰል ትዕይንት እየተመለከቱና መስጊድ ውስጥ ሸንት እየተሸና እያዩ ጓደኞቻቸውን ከእርምጃ አሰቆሙ። ምን ዓይነት ታጋሽነት ነው! ሰውዬው ጨርሶ ሱሪውን ሲታጠቅ በትህትና ጠሩት። መጣና አጠገባቸው ቆመ። "እነዚህ መስጊዶች የተገነቡት ለዚህ አገልግሎት ሳይሆን ለሶላት መስገጃና ለቁርዓን መቅሪያ ነው።" ግልጽ ምክራቸው በዚሁ ተጠናቀቀ።

ሰውዬው የነብዩን ምክር ሰምቶ ወጣ። የሶላት ሰዓት ሲደርስ መጣና ከነሱ ጋር ለሶላት ቆመ። ነብዩ "አሏሁ አክበር" ብለው ሶላቱን ጀመሩ። ቁርዓኑን ቀርተው

ተጎነበሱ። ከሩኩእ ሲነሱ "ሰሚአሏሁ ሊመን ሀሚዳ" /አላህ አመሰጋኙን ይሰማል/ አሉ። ሰሃቦችም "ረበና ወለከል ሀምድ" /ጌታችን ምስጋና ላንተ ነው/ አሉ። ያ ሰውዬ ግን "አላህ ሆይ! ከኔና ከመሐመድ በስተቀር ለሌላ ሰው አትዘን" የሚል ዓረፍተ ነገር ጨመረበት። ነብዩ ሰሙት። ሶላቱ ሲያልቅ ያን ንግግር ማን እንደተናገረው ጠየቁ። ሰሃቦችም ወደዚያ ሰው ጠቆሚቸው። ወደሳቸው እንዲጠጋ ጠየቁት። ሲያዩት የጠዋቱ ገጠሬ ነው። የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፍቅር ልቡ ውስጥ ገብቶ የአላህ እዝነት በሱና በሳቸው ላይ ብቻ እንዲወርድ አስመኘው። ነብዩም "ሰፊ የሆነውን ነገር አጠበብከው" አሉት። የአላህ እዝነት ሰፊና ለሁሉም ሰው የሚበቃ በመሆኑ ለሁለት ሰው ብቻ መወሰን የለበትም ማለታቸው ነው።

ነብዩ አቀራረባቸውን በማሳመር እንዴት ልቡን እንደተቆጣጠሩት ተመልከት። ምክንያቱም እሱ ከበረሃ የመጣ ገጠሬ ነው። የኡመርና የአቡበክር ወይም የሙዓዝና የአማር ዓይነት እውቀት እንዲኖረው አይጠበቅበትም። ስለዚህ እነሱ በሚታዩበት ዓይን ሊታይ አይችልም። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር አልፎ አልፎ ይገናኝ የነበረውን የሙዓዊያ ቢን አልሀከምን (ረ.ዐ) ሁኔታ እንመልከት። መዲና ውስጥ አልኖረም። ነብዩም በተደጋጋሚ አያገኙትም። ይልቁንም ልቡ የሚያጋድልበት የከብት መንጋ ነበረው። አንድ ቀን ሙዓዊያ መዲና መጣና የነብዩን መስጊድ ጎበኘ። ነብዩ ከባልደረቦቻቸው ጋር ቁጭ ብለው ስለማስነጠስና ደንቦቹ እየተወያዩ ነበር። አንድ ሰው ወንድሙ ካስነጠሰና አልሃምዱሊላህ ካለ የርሀሙከላህ (የአላህ እዝነት ባንተ ላይ ይውረድ) ይበለው አሉ። ሙዓዊያ ይቺን በጭንቅላቱ ይዞ ወጣ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ለሆነ ጉዳይ ወደ መዲና ይመለሳል። መስጊድ ሲገባ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ሶላት እየሰገዱ ነበር። አብሮ መስገድ ጀመረ። በመሃል አንዱ ሶሃባ አስነጠሰ። ሙዓዊያ መልሰ መስጠት እንዳለበት አስታወሰ። እናም ሰውዬው "አልሃምዱሊላህ" ከማለቱ በፊት ድምጹን ከፍ አድርጎ "የርሀሙከላህ" አለ። እየሰገዱ የነበሩት ሰዎች ግራ ተጋብተው ይገላምጡት ጀመር። ሁኔታውን ሲመለከት ግራ ተጋባና "ወይኔ ጉዴ ለምን ታፈጡብኛላችሁ?" አላቸው። ሶሃቦች ዝም በል ለማለት በእጆቻቸው ጭኖቻቸውን መምታት ጀመሩ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "የርሀሙከላህ" የሚል ንግግርና ንትርክ ሰምተዋል። ሆኖም ያን ድምጽ አያውቁትም። ሶላቱ ሲያበቃ "ማን ነው ያን ንግግር የተናገረው?" በማለት ጠየቁ። ሶሃቦችም ወደ ሙአዊያ ጠቆሚቸው። ነብዩ ወደኔ ና አሉት። ሶላት በማቋረጡና የሰዎችን ትኩረት በመበታተኑ ምን እንደሚጠብቀው ስላላወቀ በጣም ፈራ። ሙአዊያ ሲናገር "እናትና አባቴ ፊዳ ይሁኑላቸው። ወላሂ ከሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እንደሳቸው አይነት በጥሩ ሁኔታ የሚያስተምር መሪ አላየሁም። እምላለሁ፤ አልተቆጡኝም፤ አልመቱኝም፤ ወይም አላዋረዱኝም። ይልቁንም በቀላሉ ሶላት ውስጥ ከሰዎች ጋር ማውራት አይፈቀድም። ሶላት አላህን ማላቅ፣ ታላቅነቱን ማወጅና የቁርዓን ንባብን ብቻ የያዘ ነውና አሉኝ። ይህ ነበር ግልጽ ምክራቸው" ብሏል። ሙአዊያ ምክሩን ተቀበለ። ከተረጋጋ በኋላም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሰለ አንዳንድ

ተነነበሱ። ከሩኩእ ሲነሱ "ሰሚአሏሁ ሊመን ሀሚዳ" /አላህ አመሰጋኙን ይሰማል/ አሉ። ሰሃቦችም "ረበና ወለከል ሀምድ" /ጌታችን ምስጋና ላንተ ነው/ አሉ። ያ ሰውዬ ግን "አላህ ሆይ! ከኔና ከመሐመድ በስተቀር ለሌላ ሰው አትዘን" የሚል ዓረፍተ ነገር ጨመረበት። ነብዩ ሰሙት። ሶላቱ ሲያልቅ ያን ንግግር ማን እንደተናገረው ጠየቁ። ሰሃቦችም ወደዚያ ሰው ጠቆሚቸው። ወደሳቸው እንዲጠጋ ጠየቁት። ሲያዩት የጠዋቱ ገጠሬ ነው። የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፍቅር ልቡ ውስጥ ገብቶ የአላህ እዝነት በሱና በሳቸው ላይ ብቻ እንዲወርድ አስመኘው። ነብዩም "ሰፊ የሆነውን ነገር አጠበብከው" አሉት። የአላህ እዝነት ሰፊና ለሁሉም ሰው የሚበቃ በመሆኑ ለሁለት ሰው ብቻ መወሰን የለበትም ማለታቸው ነው።

ነብዩ አቀራረባቸውን በማሳመር እንዴት ልቡን እንደተቆጣጠሩት ተመልከት። ምክንያቱም እሱ ከበረሃ የመጣ ገጠሬ ነው። የኡመርና የአቡበክር ወይም የሙዓዝና የአማር ዓይነት እውቀት እንዲኖረው አይጠበቅበትም። ስለዚህ እነሱ በሚታዩበት ዓይን ሊታይ አይችልም። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር አልፎ አልፎ ይገናኝ የነበረውን የሙዓዊያ ቢን አልሀከምን (ረ.ዐ) ሁኔታ እንመልከት። መዲና ውስጥ አልኖረም። ነብዩም በተደጋጋሚ አያገኙትም። ይልቁንም ልቡ የሚያጋድልበት የኩበት መንጋ ነበረው። አንድ ቀን ሙዓዊያ መዲና መጣና የነብዩን መስጊድ ጎበኘ። ነብዩ ከባልደረቦቻቸው ጋር ቁጭ ብለው ስለማስነጠስና ደንቦቹ እየተወያዩ ነበር። አንድ ሰው ወንድሙ ካስነጠሰና አልሃምዱሊላህ ካለ የርሀሙከላህ (የአላህ እዝነት ባንተ ላይ ይውረድ) ይበለው አሉ። ሙዓዊያ ይቺን በጭንቅላቱ ይዞ ወጣ።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ለሆነ ጉዳይ ወደ መዲና ይመለሳል። መስጊድ ሲገባ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር ሶላት እየሰገዱ ነበር። አብሮ መስገድ ጀመረ። በመሃል አንዱ ሶሃባ አስነጠሰ። ሙዓዊያ መልሰ መስጠት እንዳለበት አስታወሰ። እናም ሰውዬው "አልሃምዱሊላህ" ከማለቱ በፊት ድምጹን ከፍ አድርጎ "የርሀሙከላህ" አለ። እየሰገዱ የነበሩት ሰዎች ግራ ተጋብተው ይገላምጡት ጀመር። ሁኔታውን ሲመለከት ግራ ተጋባና "ወይኔ ጉዴ ለምን ታፈጡብኛላችሁ?" አላቸው። ሶሃቦች ዝም በል ለማለት በእጆቻቸው ጭኖቻቸውን መምታት ጀመሩ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "የርሀሙከላህ" የሚል ንግግርና ንትርክ ሰምተዋል። ሆኖም ያን ድምጽ አያውቁትም። ሶላቱ ሲያበቃ "ማን ነው ያን ንግግር የተናገረው?" በማለት ጠየቁ። ሶሃቦችም ወደ ሙአዊያ ጠቆሚቸው። ነብዩ ወደኔ ና አሉት። ሶላት በማቋረጡና የሰዎችን ትኩረት በመበታተኑ ምን እንደሚጠብቀው ስላላወቀ በጣም ፈራ። ሙአዊያ ሲናገር "እናትና አባቴ ፊዳ ይሁኑላቸው። ወላሂ ከሳቸው በፊትም ሆነ በኋላ እንደሳቸው አይነት በጥሩ ሁኔታ የሚያስተምር መሪ አላየሁም። እምላለሁ፤ አልተቆጡኝም፤ አልመቱኝም፤ ወይም አላዋረዱኝም። ይልቁንም በቀላሉ ሶላት ውስጥ ከሰዎች ጋር ማውራት አይፈቀድም። ሶላት አላህን ማላቅ፣ ታላቅነቱን ማወጅና የቁርዓን ንባብን ብቻ የያዘ ነውና አሉኝ። ይህ ነበር ግልጽ ምክራቸው" ብሏል። ሙአዊያ ምክሩን ተቀበለ። ከተረጋጋ በኋላም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ) ሰለ አንዳንድ

ግላዊ ጉዳዮች ይጠይቃቸው ጀመር።

"የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ኃይማኖት የለሽ ነበርኩ። ሆኖም አላህ ኢስላምን አመጣልን። ከመካከላችን ከጠንቋዮች እርዳታን የሚጠይቁ ሰዎች አሉ። ጠንቋዮችም የማይታይን እናያለን ይላሉ። እናም ሰዎች እየሄዱ ይጠይቋቸዋል" አለ። ነብዩም "ከነሱ አትጠጋ" አሉት። ማለትም አንተ ሙስሊም ነህ። ከአላህ በስተቀር የሩቅን የሚያይ የለም።

"በገድ የሚያምኑ ሰዎች አሉ" አለ። ማለትም የወፎችን የአበራረር ሰልት በመመልከት መጥፎ እድልን የሚተነብዩ። ነብዩም "ይህ ከልቦቻቸው ላይ ሊመጣ የሚችል ሃሳብ ነው። ግና ከጉዳያቸው አይመልሳቸው" አሉት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) መስጊድ ውስጥ የተጸዳዳውንና ሶላት ላይ ያወራውን ሰው ተጨባጭ ሁኔታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ መልኩ ነው ያስተናገዱት። ምክንያቱም የነሱ ዓይነት ሰው ስህተት ሊሰራ ይችላል።

መዓዝ (ረ.ዐ) ኢሻን ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ይሰግድና ህዝቦቹን ለማሰገድ ወደ ሌላ መስጊድ ይሄድ ነበር። ሁለተኛው ሶላት ለሱ ሱና ሲሆን ተከትለውት ለሚሰግዱት ሰዎች ግን ፈርድ ነው። ከእለታት አንድ ቀን ማታ መዓዝ እንደተለመደው ከነብዩ ጋር ሰግዶ ወደ ህዝቦቹ ሄደ። መስጊድ ገባና ሶላቱን ጀመረ። አንድ ወጣት መጣና ጀመዓውን ተቀላቀለ። ልክ ፋቲሀን እንደጨረሰ ሱረቱል በቀራን መቅራት ጀመረ። ሰዎች ቀኑን ሙሉ ከግብርና ስራና ከከብቶች ጋር ሲለፉ ይውላሉ። እናም ከእንቅልፍ ጋር እየታገሉ ነው የኢሻን ሶላት የሚጠባበቁት። ያ ወጣት ሶላቱ በጣም ረዘመበት። ራሱን ከጀመዓው ነጠለና ሶላቱን በራሱ ጨርሶ ወደ ቤቱ ሄደ።

መዓዝ ሲጨርስ ሰዎች መጡና "መዓዝ ሆይ! እከሌ እከሌ ከኛ ጋር እየሰገደ ነበር። ሆኖም ሶላቱ ሰለረዘመበት ትቶ ሄደ" አሉት። መዓዝ በጣም ተናደደና "የመናፍቅነት በሽታ አለበት ማለት ነው። ይህንን ነገር ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አሳውቃለሁ" አለ። ሰዎቹም መዓዝ የተናገረውን ነገር ወስደው ለወጣቱ ነገሩት። እሱም "እኔም እሱ የሚሰራውን ነገር ለነብዩ እነግራቸዋለሁ" አለ። ሁለቱም ነብዩ ዘንድ ሄዱ። መዓዝ ወጣቱ የፈፀመውን ድርጊት ተናገረ። ወጣቱም "የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! እዚህ እርሰዎ ጋር ብዙ ይቆያል። እኛም ጋ ከመጣ በኋላ ሶላት ላይ ብዙ ያቆዬናል። ወላሂ የአላህ መልዕከተኛ መዓዝ ሶላት በጣም እንደሚያስረዝም ስለምናውቅ ዘግይተን ነው ወደ ሶላት የምንመጣው" አለ። ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ) "የትኛውን ሱራ ነው የምትቀራው?" በማለት ጠየቁት ለመዓዝ። ሱረቱል በቀራንና ሌሎች ረጃጅም ምዕራፎችን እንደሚቀራ ነገራቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ)

መዓዝ በማርዘሙ ምክንያት ሰዎች ወደ ሶላት ዘግይተው እንደሚመጡ ሲሰሙ በጣም ተቆጡ። ሰዎች ሶላት ላይ ለምን እንደሚሰላቹም አወቁ። ለመዓዝም "መዓዝ ሆይ! አንተ ችግር ፈጣሪ

ነህ እንዴ?" አሉት። ሰዎችን እያስቸገርከ ለምን ከኃይማኖቱ ታርቃለህ? ወሰማኢ ወጢሪቅን፣ ወሰማኢ ዛቲል በሩጅን፣ ወሸምሲ ወዱሃሃን እና ወለይሊ ኢዛ የማሻን ቅራ ማለታቸው ነው። ለወጣቱም ትህትና በተሞላበት ሁኔታ "ሶላት ላይ ምንድን ነው የምታደርገው የወንድሜ ልጅ?" አሉት።

"ፋቲሀን እቀራለሁ። ከዚያም አላህ ጀነትን እንዲለግሰኝና ከጀሃነም እንዲጠብቀኝ አለምነዋለሁ" አለ። ኑብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ረጃጂም ዱዓዎችን ሲያደርጉና ሙዓዝም ተመሳሳዩን ሲያደርግ መስማቱን በማስታወስ "እርስዎና ሙዓዝ ምን እንደሚያነበንቡ አላውቅም" አለ። ምን ዓይነት ረጂም ዱዓ እንደምታደርጉ አላውቅም ማለቱ ነው። ኑብዩም "ሙዓዝና እኔ የምናደርገው ተመሳሳይ ዱዓ ነው" ሲሉ መለሱለት። ማለትም ስለ ጀነትና ጀሀነም ነው ዱዓዎችን የምናደርገው። ሙዓዝ በሙናፊቅነት ስለከሰሰው ወጣቱ በጣም ተሰምቶት ስለነበርም "ጠላቶች እየደረሱ ነው የሚል ወሬ በሚመጣበት ቀን ሙዓዝ ያያል" አለ። በአላህ መንገድ በጂሃድ ላይ ምን እንደምሰራ ለሙዓዝ አሳየዋለሁ። ሙናፊቅ ነህ እንዳለኝ አይቀርም። ያኔ እምነቴ ይገለፅሊታል ማለቱ ነው።

ብዙም ሳይቆይ ጦርነት ተነሳና ወጣቱ መስዋዕት ሆነ። ኑብዩ ይህን ሲሰሙ ለሙዓዝ "ሙዓዝ ሆይ! ባላንጣህ እንዴት ሆነ?" ማለትም በንፍቅና የከሰሰከው ሰው እንዴት ሆነ አሉት። ሙዓዝም "የአላህ መልዕከተኛ ሆይ! አሱ እውነተኛ ሰው ነው። ሙናፊቅ አይደለም። በአላህ መንገድ ተሰውቷል" አላቸው።

የሰዎች ተፈጥሮና ደረጃ እንዴት እንደሚለያይ ተመልከት። ኑብዩ እንዴት ያስተናግዷቸው እንደነበርም አስብ።

አንድ አስተያየት

ሰዎች ተመሳሳይ ተፈጥሮ ይኖራቸዋል ብለህ አታስብ። ይልቁንም በብዙ ነገሮች ይለያያሉ።



ትክክለኛውን ርዕሰ ምረጥ

ከባለፈው ርዕሰ የሚቀጥለው ሰዎችን እንዴት እናናግራለን፤ ስለ ምን እናናግራለን የሚለው ርዕሰ ጉዳይ ነው። አንድ ሰው ከሌላኛው ጋር ሲወያይ ተስማሚ የሆኑ ርዕሶችን መምረጥ አለበት። ለወጣቶች የሚመረጠው ርዕሰ ለአዛውንቶች ከሚመረጠው ርዕሰ የተለዬ መሆን አለበት። ከተማረ ሰው ጋር የሚደረግ ውይይት ካልተማረው ጋር አንድ አይነት መሆን የለበትም። በተመሳሳይ ለሚስቶቻችን የምንጠቀማቸው ቃላት ከእህቶቻችን ጋር ከምንጠቀማቸው የተለዩ መሆን አለባቸው። ይህም ማለት ለእያንዳንዱ ሰው ሙሉ በሙሉ የተለያየ ርዕሰ ይሁን ማለት አይደለም። ለእህት የሚነገር ጉዳይ ለሚስት አይነገርም። ለወጣት የሚነገር ጉዳይ ለአዛውንት አይነገርም ማለት አይደለም። ታሪኩን የምንናገርበት መንገድ ይለያያል።

ለምሳሌ ያህል አንድ ወጣት አያቱን ሊዘይሩ ለመጡ ከሰባ ዓመት በላይ ለሆናቸው ሰዎች ከጓደኞቹ ጋር የባህር ዳርቻ ላይ እንዴት እንደ ተዝናና ወይም ጓደኛው እንዴት ጥሩ እግር ኳስ ተጫዋች እንደሆነ እያወራ ቢሰቅና ቢቀልድ ተገቢ ነው? በጭራሽ ተገቢ አይደለም። በተመሳሳይ ለህፃናት ባል ሚስቱን እንዴት መያዝ እንዳለበት አናወራቸውም። ስለዚህ የሚፈልጉትን ርዕሰ መምረጥ ሰዎችን ከመሳቢያ ዘዴዎች አንዱ ነው።

ለምሳሌ ጎበዝ ልጅ ያለው አባት ካለ ስለ ልጁ ሁኔታ ልንጠይቀው ግድ ነው። ምክንያቱም አባት በልጁ ስለሚኮራና ስለ ጉዳዩ ማውራት ስለሚወድ። በተመሳሳይ አንድ በቅርቡ ሱቅ ከፍቶ ጥሩ እንቅስቃሴ እያደረገ ያለን ሰው ስለ ሱቁና ስለ ደንበኞቹ መጠየቅ ያስፈልጋል። ምክንያቱም ሰውዬውን ያስደስተዋል።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህን ጉዳይ ከግንዛቤ የሚያስገቡ ሰው ነበሩ። በመሆኑም ለወጣቶች የሚናገሩት ለአዛውንቶች ከሚናገሩት የተለዬ ነው። ለሕፃናት የሚናገሩት ለሴቶች ከሚናገሩት የተለዬ ነበር። ጃቢር ኢብኑ አብዱላህ ታላቅ ሶሃባ ነበር። ኡሁድ ጦርነት ላይ አባቱ ተገደለ። ዘጠኝ እህቶቹን ይዞ ብቻውን ቀረ። አባቱ ብዙ ዕዳ ነበረበት። ይህ ሁሉ ኃላፊነት በለግላጋው ወጣት ትከሻ ላይ ወደቀ። በመሆኑም ጃቢር ዘወትር ስለ እህቶቹና ጠዋት ማታ ስለሚጨቀጭቁት አበዳሪዎች እዳ

ያስባል፤ ይጨነቃል። ጃቢር በዛት አል ሪቃ ዘመቻ ወቅት ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ተጓዘ። የሚጋልባት ግመል በጣም ደካማና መራመድ ያቃታት ነበረች። ደህና ግመል የሚገዛበት ገንዘብ አልነበረውም። በመሆኑም ከሰው ሁሉ ወደ ኋላ ቀረ። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጦሩ ኋላ ላይ ነበሩና ጃቢርን አገኙት። ነብዩም "ጃቢር ምን ችግር ኢጋጠመህ?" ሲሉ ጠየቁት።

"ግመሌ ወደ ኋላ አስቀረችኝ" አላቸው። ነብዩም "መሬት ላይ አስቀምጣት" አሉት። አስቀመጣት። ጅራፍህን ወይም አንድ የዛፍ ቅርንጫፍ ቆርጠህ ስጠኝ አሉት። ሰጣቸውና ቀስ ኢድርገው መታ አደረጓት። ግመሏ ነቃ ብላ ተነሳች። ጋለባትና በደስታ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ይጓዝ ጀመር። ግመሏ ጠንካራ ሆነችለት። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጃቢር ጋር ውይይት ጀመሩ። ከሱ ጋር ለማውራት ምን ዓይነት ርዕስ መረጡ? ጃቢር ወጣት ነው። ወጣቶች ስለ ትዳርና ስለ ኢኗኗራቸው ማውራት ይወዳሉ። እናም "ጃቢር ሆይ! አግብተሃል?" አሉት።

"አዎ" ሲል መለሰ።

"ልጃረገረድ ወይስ አግብታ የፈታች?" አሉት። "አግብታ የፈታች" አላቸው።

ነብዩም በዚህ እድሜው አግብታ የፈታች ሴት ማግባቱ ገርሟቸው፡- "ለምን ልጃገረድ አላገባህም?" አሉት።

"የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አባቴ በኡሁድ ጦርነት ላይ ተሰውቷል። ዘጠኝ ሴት ልጆችን ትቶብኝ ነው የሞተው። እኔም በእነሱ እድሜ ያለች ትንሽ ልጅ አምጥቼ መጨመር አልፈለግኩም። ይልቁንም እንደ እናት እንድትሆንላቸው በማሰብ እድሜዋ ከፍ ያለ ሴት ማግባትን መረጥኩ" አለ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እያወሩት ያለው ለእህቶቹ ሲል የራሱን ደስታ አሳልፎ የሰጠ ሰው መሆኑን ተረዱ። ስለሆነም በሱ ዕድሜ ላለ ወጣት የሚሆን ቀልድ ሊነግሩት ፈለጉ። "ምናልባትም ወደ መዲና ተቃርበን ሳራር ላይ (ከመዲና አምስት ኪሎ ሜትር) ስንደርስ ነው ሚስትህ እየመጣህላት መሆኑን ሰምታ ትራሶችን የምታዘጋጀው" አሉት። ይህም ማለት ምንም እንኳ አግብታ የፈታች ብትሆንም ሁሌም ሙሽራህ ናት። በመመለስህ ትደሰታለች። ምንጣፏን አንጥፋ ትራሶቿን አስተካክላ በጉጉት ትጠብቅሃለች ማለታቸው ነው። ጃቢር ድህነቱን አሰበና "ትራስ!? የአላህ መልዕክተኛ ወላሂ ትራስ የለንም" አላቸው። ነብዩም "ኢንሻ አላህ በቅርቡ ትራስ ይኖርሃል" አሉት።

"ጃቢር" አሉት።

"ምን ልታዘዝ የአላህ መልዕክተኛ!" አለ። ነብዩም "ይህቺን ግመል ትሸጥልኛለህ?" በማለት ጠየቁት። ይህቺ ግመል ለጃቢር ሁበቱ ናት። ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ደካማ የነበረች ቢሆንም አሁን በጣም ጠንካራ ሆናለች። ሆኖም ለነብዩ ጥያቄ አሉታዊ መልስ መስጠት ተገቢ አይደለም። እናም "የአላህ መልዕክተኛ ስንት ይገዙኛል?" አላቸው።

"አንድ ዲርሃም" አሉት።

"አንድ ዲርሃም! የአላህ መልዕክተኛ እየቀለዱብኝ ነው አይደል?" አለ። ነብዩም "ሁለት ዲርሃም" አሉ።

"አሁንም እየቀለዱብኝ ነው የአላህ መልዕክተኛ" አላቸው። የአንድ ውቄት ወርቅ ዋጋ ወይም አርባ ዲርሃም እስኪደርስ ድረስ ዋጋውን እየጨመሩ ሄዱ። ጃቢርም "እሺ መዲና እስክደርስ ድረስ ግን ኢጋልባታለሁ" አለ። ነብዩ ተስማሙ።

መዲና ሲደርሱ ጃቢር ቤቱ ሄደና የግመሏን ጭነት አወረደ። ከዚያም ሶላት ሊሰግድ ሲሄድ ግመሏንም ይዞ ሄደ። ሰግደው ሲወጡ "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይኸውልዎ ግመልዎ" አላቸው። ነብዩም "ቢላል ሆይ! ከአርባ ዲርሃም ላይ የተወሰነ ጨምረህ ስጠው" አሉት። ቢላል ገንዘቡን ሰጠው። ጃቢር ገንዘቡን ተቀብሎ በዚህ ገንዘብ ምን ላድርግበት? ግመል ልግዛበት ወይስ የቤት ዕቃ? በማለት እያሰላሰለ ወጣ። ነብዩም ወዲያውኑ "ቢላል ሆይ! ግመሏን ውሰድና ለጃቢር ስጠው"አሉት። ቢላል ግመሏን ይዞ ጃቢርን ፍለጋ ወጣ። አገኘውና "ግመሏን ውሰድ" አለው።

"ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ?" አለ ጃቢር ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሸያጩን ውል ሳያፈርሱ እንዳልቀረ እያሰበ። ቢላልም "የአላህ መልዕክተኛ ግመሏንም ብሩንም እንድትወስድ ፈቅደውልሃል" አለው። ጃቢር ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተመለሰና ምን እንደተፈጠረ ጠየቃቸው። "ግመልህን ለመውሰድ ካንተ ጋር በዚህ መልኩ የምደራደር ይመስልሃል?" አሉት። ግመሏን ለመግዛት ከፈለኩ ዋጋ እንድትቀንስልኝ አልጠይቅህም ነበር? ጥቂት ገንዘብ በመስጠት ላግዝህ ስለፈለኩ ነው ይህን ያደረግኩት ማለታቸው ነው። ምን ዓይነት ድንቅ ባህሪ ነው! ከወጣቱ ጋር ለመወያየት ጥሩ ርዕስ መረጡ። ሊረዱት ሲወስኑ ደግሞ በታላቅ ርህራሄና ፍቅር አደረጉት።

አንድ ቀን ጁላይቢብ የተባለ ወጣት ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጠገብ ቁጭ ብሎ ነበር። ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ታላላቅ ሶሃባዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን ድሃና መልከ ጥፉ ሰው ነበር። ከዚህ ላጤ ወጣት ጋር ለመወያየት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምን ዓይነት ርዕስ ቢመርጡ ጥሩ ነው? ስለ አረብ ዝርያዎችና የትኛው ከየትኛው ይበልጥ የተከበረ ስለመሆኑ? ስለ ገቢያና ስለ ሽያጭ ህጎች? አይደለም? ይልቁንም ጁላይቢብ ለሱ